አማርኛ Amharic

ለምግብ አገልግሎት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

ሪሳይክል ማድረግ፥ የሲያትል ንግድ ድርጅቶች ሪሳይክል የሚደረጉ ነገሮችን በቆሻሻ መጣያ ውስጥ መጣል አይፈቀድላቸውም።

ለብስባሽ ማዘጋጀት (ኮምፖስት)፥ የሲያትል ንግድ ድርጅቶች ለብስባሽ ሊዘጋጁ የሚችሉ ነገሮችን በቆሻሻ መጣያ ውስጥ መጣል አይፈቀድላቸውም።

ማሸጊያ፥ የሲያትል የምግብ አገልግሎት ንግድ ድርጅቶች ወደ ብስባሽ ሊቀየሩ የሚችሉ ወይም ሪሳይክል የሚደረጉ የምግብና የለስላሳ መጠጦች ማሸጊያ መጠቀም ይኖርባቸዋል።

ሪሳይክል የሚደረጉ ነገሮች በቆሻሻ መጣያ ውስጥ እንዲጣሉ አይፈቀድም፥ የሲያትል ማዘጋጃ ቤት ደንብ (21.36.083)
ሁሉም የንግድ ድርጅቶች ወረቀቶችን፣ ባኮዎችን፣ ጠርሙሶችንና የጠርሙስ ማሶሮዎችን፣ የላስቲክና የወረቀት ኩባያዎችን፣ የላስቲክ ጠርሙሶችንና ማሶሮዎችን፣ ከአሉሚንየምና ከቆርቆሮ የተሰሩ ጣሳዎችን እና የጓሮ ጥራጊዎችን ከቆሻሻ መለየት ይኖርባቸዋል። እነዚህ ነገሮች በቆሻሻ መጣያ ውስጥ መጣል የለባቸውም (ከሐምሌ 1, 2014 ጀምሮ)።

ምግብ በቆሻሻ መጣያ ውስጥ መጣል አይፈቀድም፥ የሲያትል ማዘጋጃ ቤት ደንብ (21.36.082)
የንግድ ድርጅቶች ሁሉ ሁሉንም ምግብና ምግብ የነካካቸውን በኬሚካል ያልተለሰነ ወረቀቶችን፣ እንደ ናፕኪን፣ የወረቀት ፎጣዎችና የፒሳ ባኮዎች የመሳሰሉትን፣ ከቆሻሻ መለየት ይኖርባቸዋል። እነዚህን ነገሮች በቆሻሻ መጣያ ውስጥ መጣል ክልክል ነው (ከጥር 1, 2015 ጀምሮ)።

የምግብ ማሸጊያ መመሪያዎች፥ የሲያትል ማዘጋጃ ቤት ደንብ (21.36.086)

1. **እምግብ ቤት መመገብ፥** አንድ ግዜ በሚያገለግሉ ማስቀመጫዎች ምግብ የሚሸጡ ወይም የሚያቀርቡ ምግብ ቤቶች እና የምግብ አገልግሎት አቅራቢ ንግድ ድርጅቶች፣ ምግብ ቤታቸው ውስጥ ለሚመገቡ ደንበኞች፣ ወደ ብስባሽ ሊቀየሩ በሚችሉ የምግብ ማስቀመጫዎች ምግብ ማቅረብ ይኖርባቸዋል። የላስቲክ ወይም በላስቲክ የተለሰኑ የወረቀት ምርቶችን ምግብ ቤት-ውስጥ ለመመገቢያ መጠቀም የሚቻለው ጥቅም ላይ ከዋሉ በኋላ ሪሳይክል ለማድረግ እንዲቻል በደንብ ንጹህ ከሆኑ ብቻ ነው።

2. **ምግብ ይዞ-ለመሄድ፥** ምግብ ይዞ-ለሚሄድ የሚያገለግል ማስቀመጫ ሪሳይክል የሚደረግ ወይም ወደ ብስባሽ የሚቀየር ዓይነት ሊሆን ይችላል። (ከሐምሌ 1, 2010 ጀምሮ)።

3. **የተከለከሉ ነገሮች፥** የንግድ ድርጅቶች ከፕላስቲክ የተሰሩ የፎም (Styrofoam™) ማስቀመጫዎችን እንዳይጠቀሙ ተከልክለዋል። (ከጥር 1, 2009 ጀምሮ)።

ሪሳይክል የሚደረጉና ወደ ብስባሽ ሊቀየሩ የሚችሉ ነገሮችን ከቆሻሻ መጣያ ጉዳጓዶች ማስወገድ፣ ብክነትንና ብከላን ይቀንሳል። የንግድ ድርጅቶች፣ ሪሳይክል የሚደረጉ ወይም ወደ ብስባሽ ሊቀየሩ የሚችሉ ነገሮችን መጠቀም ከመጀመሩ፣ የቆሻሻ ማንሻ አገልግሎታቸውን ሊቀንሱና ገንዘብም ሊቆጥቡ ይችላሉ። ወደ ብስባሽ ሊቀየሩ የሚችሉ መገልገያ እቃዎችን ብቻ የሚጠቀሙ የንግድ ድርጅቶች፣ እቃዎቹን በቀላሉ፣ በቀጥታ ወደ ብስባሽ ማጠራቀሚያ ገንዳ ውስጥ ለመጣል ቀላል ይሆንላቸዋል።

የ Seattle Public Utilities Green Business Program ን ያነጋግሩ፣ እነዚህን መመሪያዎች ለማክበር የነጻ እርዳታና መርጃ ምንጮችን ለማግኘት።

For interpretation services, please call 206-684-3000.
如需要口譯服務，請撥電話號碼 206-684-3000.
통역 서비스를 원하시면 206-684-3000. 으로 전화하세요.
Wixii turjubaan afka ah ku saabsan, Fadlan la soo xariir taleefoonka: 206-684-3000.
Para servicios de interpretación por favor llame al 206-684-3000.
Para sa serbisyo ng tagapagpaliwanag, tumawag sa 206-684-3000.
Vè dịch vụ phiên dịch xin gọi 206-684-3000.

Seattle Public Utilities

greenbusiness@seattle.gov www.seattle.gov/util/GreenYourBusiness 206-343-8505

FC2/3-15

የ ም ግ ብ አ ገ ል ግ ሎ ት ን ግ ድ ድ ር ጅ ቶ ች

አማርኛ Amharic

የነጻ መርጃ ምንጮች

በነጻ ፖስተሮችንና የማጠራቀሚያ ገንዳ ተለጣፊ ጽሁፎችን (ሌብል) እንዲሰጥዎት ይጠይቁ ወይም የራስዎን ፖስተሮች ከዚህ ድረገጽ ያዘጋጁ፡ www.seattle.gov/util/ForBusinesses/SolidWaste/FoodYardBusinesses/Commercial/WastePosterOrderForm.

በምግብ ቤት የመመገቢያ ቦታ (ለሦስት የተመደበ)

ከምግብ ቤት ኩሽና የተሰበሰበ
(በተለያዩ ቋንቋዎች ተዘጋጅቷል)

የማጠራቀሚያ ገንዳ ተለጣፊ ጽሁፎች

የመሰብሰቢያ አገልግሎት አቅራቢዎች

RECOLOGY CLEANSCAPES	WASTE MANAGEMENT	REPUBLIC	CEDAR GROVE	SEADRUNAR
ቆሻሻ | ሪሳይክል ማድረግ | ለብስባሽ ማዘጋጀት	ቆሻሻ | ሪሳይክል ማድረግ | ለብስባሽ ማዘጋጀት	ሪሳይክል ማድረግ | ለብስባሽ ማዘጋጀት	ሪሳይክል ማድረግ | ለብስባሽ ማዘጋጀት	ሪሳይክሊንግ
206-250-7500	800-592-9995	206-332-7777	877-994-4466	206-467-7550
info@recologycleanscapes.com	recyclenw@wm.com	infoseattle@republicservices.com	help@cgcompost.com	info@seadrunarrecycling.com

የአገልግሎት አቅራቢ መረጃ

ስለ ማሸጊያ፣ ማጠራቀሚያ ገንዳ እና አገልግሎት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የ Seattle Public Utilities Green Business Program ን ያነጋግሩ።

ማሸጊያ

ወደ ብስባሽ ሊቀየሩ የሚችሉና ሪሳይክል የሚደረጉ ማሸጊያዎች አቅራቢዎችና አምራቾች አድራሻ።

የመሰብሰቢያ ገንዳዎች

የእቤት ውስጥ ማጠራቀሚያ ገንዳዎች አቅራቢዎችና አምራቾች አድራሻ።

የመሰብሰቢያ አገልግሎቶች

ወደ ብስባሽ ሊቀየሩና የሚችሉና ሪሳይክል የሚደረጉ ነገሮችን ለመሰብሰብ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች አድራሻ።

greenbusiness@seattle.gov www.seattle.gov/util/GreenYourBusiness 206-343-8505

FC2/3-15